ቴሌግራም፡ @giziew7 | ስልክ፡ 0949-61 11 11 | 0717-96 43 73 | email: editor@giziew.org | fb.me/giziew7 | YouTube: @Giziew | https://www.giziew.org/

የትምህርቱ ዋና ሓሳቦች
በሰማይ የጀመረውና ወደ ምድር የወረደው ታላቁ ተጋድሎ መልኩን በተለያየ ሁኔታ የቀያየረ
ቢመስልም ዋናው ዓላማ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው የእግዚአብሔርን አፍቃሪነት በሰዎች
ልብ ውስጥ ቦታ እንዳይኖረው ማድረግ ነው፡፡ በተለይ “ሁለቱ ምስክሮች” በሚል ርዕስ በምናጠናው
በዚህ ትምህርት እነዚህ ምስክሮች ለ1,260 ዓመታት (ሦስት ዓመት ተኩል) ማቅ ለብሰው እንዴት
ሲመሰክሩ እንደነበር በስፋት እንዳስሳለን፡፡ በዘካርያስ 4፡14 መሠረት እነዚህ ምስክሮች የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ በቃሉ እና ቃል በሆነው በክርስቶስ መካከል በንጽጽር የምናያቸው ነጥቦች ይኖራሉ፤ ለምሳሌ ጌታችን ከራሱ ሕዝብ ይደርስበት የነበረውን መከራና ስቃይ ለ3 ዓመት 1/2 ተቋቁሟል፤ የእግዚአብሔር ቃልም እንዲሁ ራሳቸውን የሃይማኖት መሪዎች ነን በሚሉ ለሦስት ዓመት ተኩል (1,260 ዓመት) እንዳይነበብ፣ እንዳይተረጎምና እንዳይሰራጭ ተደረገ፡፡ ልክ ጌታችን እንደሞተና እንደ ተነሳ ሁለቱ ምስክሮችም ይሞታሉ ከዚያም ይነሳሉ፡፡ ክርስቶስ አሸናፊ እንደሆነው ሁሉ ቃሉም እንዲሁ አሸናፊ ነው፡፡ ሕዝቡም እንዲሁ በክርስቶስና በቃሉ አሸናፊዎች ይሆናሉ፡፡ የዚህ ሳምንት ትምህርት በሁለት ዐበይት ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡-
1. በራዕይ 11 የተጠቀሱት ሁለቱ ምስክሮች
• የሚያመለክቱት መጽሐፍ ቅዱስን ነው
• በስደት ዘመንም አገልግሎት ሰጥተዋል፤ ይህም

• ከ538-1798ዓም በነበረው የጨለማ ዘመን ነው (1,260 ዓመት)
2. የ1,260 ትንቢት ዘመኑ ሲያበቃ፤
• ሁለቱ ምስክሮች ይገደላሉ
• ጌታ እንደተነሳው ከሞት ይነሳሉ፤ ይህም
• እግዚአብሔር በክርስቶስ እና በቃሉ የታላቁ ተጋድሎ አሸናፊነቱን የሚያመለክት ነው

6ኛ ትምህርት፤ ሁለቱ ምስክሮች

1.የሁለቱ ምስክሮችን ባሕርያት በዝርዝር እንመልከት
• በራዕይ 11 “ሁለት ምስክሮች” የተባሉት እነማን ናቸው?
• ዮሐንስ በራዕይ 11 “ሁለት ምስክሮች” ብሎ ከጠራቸው ምን እንማራለን?
• ምስክሮቹ የመሰከሩበት ዘመን ማን ይባላል? ምን ያህል ጊዜ ቆየ?
• በዘካርያስ 4፡1-6 የተጻፈው ስለ ሁለቱ ምስክሮች ምን ይነግረናል?

• ሁለቱ ምስክሮች ጨለማን እንዴት መግፈፍ ቻሉ? (መዝ 119፡1-5፣ 130)
• ብሉይን ከሐዲስ መነጠል አግባብ የማይሆነው ለምንድነው? (ሉቃ 24፡25-
27፣ 44-45፣ 2ኛ ጢሞ 3፡16-17)
2. ትንቢታዊ የጊዜ ቀመር
• በራዕይ 11፡3 የተጠቀሰው ዘመን ምን የሚያመለክት ነው?
• ሁለቱ ምስክሮች ማቅ ለብሰው በሚመሰክሩበትን 1,260 የትንቢት ቀናት
ከእነዚህ ጥቅሶች ጋር ያነጻጽሩ፤ ራዕይ 12፡5-6፤ 14-15፤ 13፡5 እና ዳን 7፡25
• ምስክሮቹ ማቅ መልበሳቸው ምን ያመለክታል?
3.የሁለቱ ምስክሮች መገደል
• በ18ኛው ክዘ መገባደጃ ሁለቱ ምስክሮች እንዲገደሉ ያደረገ ምን ነገር
ተከሰተ? (ራዕይ 11፡7-9)
• በራዕይ 11፡8-10 ባለው ክፍል የተወሳው ምን የሚያመለክት ነው?
• በዘመናችን ሰዎች እንዴት ነው ሁለቱን ምስክሮች እየገደሉ ያሉት?
• ሐዋርያት ስለ እግዚአብሔር ቃል መከራ ሲደርስባቸው መልሳቸው ምን
ነበር? (ሐዋ 5፡41-42)
• በፈረንሳይ አብዮት የታላቁ ተጋድሎ ተጽዕኖ እንዴት ነው የተገለጸው?

4.የሁለቱ ምስክሮች በትንሣኤ መነሳት
• በራዕይ 11፡11 መሠረት ስለ ተገደሉት ምስክሮች የተነገረው ትንቢት ምን
የሚል ነበር?
• በ19ኛው ክዘ ለሁለቱ ምስክሮች ሕይወት የሚሰጥ ምን ተከሰተ?
(የሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ፣ ሁለተኛው ታላቁ መነቃቃት)
• ከምስክሮቹ ትንሣኤ ምን እንማራለን?

5. የሁለቱ ምስክሮች ምስክርነት፤
• ለሁለቱ ምስክሮች በአሁኑ ዘመን የተሰጠው ተልዕኮ ምንድነው? (ራዕይ
14፡6፤ ማቴ 24፡14)
• በራዕይ 11፡15-18 መሠረት ሁለቱ ምስክሮች ሥራቸውን ሲጨርሱ
የተከሰተው ኩነት ምንድነው?
• ባለንበት ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ዱሮው አይከለከልም፤ ከስልካችን
ጀምሮ በየቦታው አለ፤ ይህ መሆኑ ያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድነው?
• አንዳንድ ሰዎች ብሉይ ኪዳን ጥላ ነው፤ አያስፈልግም፤ ዘመናችን የሐዲስ
ነው ይላሉ፤ የብሉይን አስፈላጊነት እንዴት መረዳት እንችላለን?

ታላቁ ተጋድሎ

የ6ኛ ትምህርት መምሪያ የትምህርቱ መሪ ጥቅስ፤ ኢሳይያስ 40፡8